# «እኔ በበኩሌ . . .»

ጊዜው ቢረዝምም በሕጻንነት ዕድሜ በውስጣችን የተቀረጹ ትዝታዎች ሁልጊዜም አብረውን ይኖራሉ። በተለይ ጣፋጭ የሆኑ ትዝታዎች አብረውን ያድጉና ሁልጊዜም ከሕሊናችን አይርቁም። እኔም እንደሌሎች አንድ ጣፋጭ የሕጻንነት ትዝታ አለኝ። ምናልባት የሁለት ወይም የሶስት ዓመት ሕጻን ልጅ ብሆን ነው። ቴፕሬከርዱ ላይ ተቀምጦ የሚሽከረከረውንና በቅባት የተወለወለ የሚመስለውን የሙዚቃ ሸክላ ለሕጻን ልጅ ብቻ በተቸረ አድናቆትና ጉጉት ተመስጬ እመለከትና አዳምጥ እንደነበረ አስታውሳለሁ። በሚገባ ራሴን ችዬ መቆምና መራመድ በማልችልበት በዚያ ለጋ ዕድሜ ላይ ሆኜ በዚያች ቅጽበት የሰማሁት ዜማ ከነቃላቱ አሁንም ትዝ ይለኛል . . .

**የዘንባባ ማር ነሽ ወለላሽ የረጋ**
**አልደርስብሽ አልኩኝ አሀሀ እጄን ብዘረጋ . . .**

አልረሳሁትም!  አልረሳውም! የኢትዮጵያ ሙዚቃ ጉዳይ ሲነሣ ያ በልጅነቴ ለመጀመሪያ ጊዜ ማዳመጤ ትዝ የሚለኝና አእምሮዬ ላይ ተቀርጾ የቀረው ጣዕመ ዜማ ጭንቅላቴ ውስጥ ይመላለሳል። ከዚያች የጨቅላ ዕድሜ ገጠመኜ ጀምሮ ይመስለኛል ለጥላሁን ገሠሠና ለሙዚቃ ሥራዎቹ ታላቅ ፍቅርና አክብሮት ያደረብኝ። በለጋው የጨቅላነት ዕድሜዬ በውስጤ የተቀረጸው የጥላሁን ገሠሠ ድምፅና ድንቅ የሙዚቃ ተሰጥኦ፥ ለእርሱም የነበረኝ አድናቆትና አክብሮት አብሮኝ አድጎ፥ አብሮኝ ኖሮ እነሆ ዛሬ የጥላሁን ገሠሠን ከዚህ ዓለም መለየት ሰማሁ። ዜናውን ከቢቢሲ ዌብሳይት ላይ እንዳነበብኩ ወዲያውኑ ሃዘን አልተሰማኝም። ምናልባት ሃዘኔን ድንጋጤ አሸንፎት ሊሆን ይችላል። ምናልባትም ደግሞ  ጥላሁን ገሠሠ በሕይወት ኖረም አልኖረ በኢትዮጵያውያን ልብ ውስጥ ሕያው ሆኖ የሚኖር ታላቅ ሰው መሆኑን ለዓመታት ራሴን በማሳመኔ ይሆናል። ብቻ መደንዘዝ አይሉት አለማመን ምን እንደሆነ ባይገባኝም ዕንባ ወዲያውኑ አላሸነፈኝም . . . ትንሽ ቆይቶ አልቀረልኝም እንጂ! ዕንባዬን ቀድሞ ግን አንድ የጥላሁን ገሠሠ ዘፈን ውስጤን ማናወጡ አልቀረም . . .

**ለተራበ አጉራሽ ላጣ ሰው ደጋፊ**
**ሲሆን ያሳዝናል እንዳፈር ረጋፊ**
**የሚመለስ ቢሆን እንደሞተ ሳይቀር**
**ያሰኛል አንዳንዱን ዳግመኛ ቢፈጠር**
**ሞት እንኳን ጨክኖ ወስዶ ከሚያስቀረው**
**ምናለ ደጋጉን ዳግመኛ ቢፈጥረው . . .**
**የሠራም ላገሩ ያልሠራም ሰነፉ**
**ያስኬዳል መንገዱ ለሞት ሲሰለፉ**
**ሞት ምርጫን ባወቀ እንዴት በወደድነው**
**ስንዴን ከእንክርዳዱ ለይቶ ቢያስቀረው**
**ሞት እንኳን ጨክኖ ወስዶ ከሚያስቀረው**
**ምናለ ደጋጉን ዳግመኛ ቢፈጥረው . . .**

የምወደው የወንድ አያቴ መጀመሪያ፥ ከዚያም ከዓመታት በኋላ ደግሞ  ውድ አባቴ ባረፉባቸው ከባድ የሃዘን ወቅቶች ይህንን ዘፈን ለብቻዬ ለራሴ እያዜምኩ ዕንባዬን አፈስ ነበር። ለነገሩ በጥላሁን ገሠሠ ዘፈን ማን ያልተነካ ሰው አለ?!

የጥላሁን ገሠሠ ዘፈኖች መልእክት ሙሉ በሙሉ ገብቶኝ ይሁን ወይም ደግሞ ለሥነግጥም ልዩ ፍቅር ስለነበረኝ ምክንያቱን በትክክል በማላውቀው ሁኔታ ከልጅነቴ ጀምሮ አብዛኛዎቹን ዘፈኖቹን ቃል በቃል አውቃቸው ነበር። ከጥላሁን ገሠሠ ድምፅ በስተጀርባ ያሉትም ታላላቅ የግጥምና የዜማ ደራስያን ሁልጊዜም ያስደንቁኛል። የጥላሁን ገሠሠ  ዘፈኖች ዘፈን ብቻ አይደሉም . . . ፍልስፍናን፥ ምክርን፥ ጥበብን፥ አዋቂነትን፥ ማስተዋልን፥ ፍትኅን፥ በጎነትን፥ ነፃነትን፥ አንድነትን፥ ፍቅርን፥ ሰላምን የተላበሱ ወርቅ የሥነጥበብ ሥራዎች እንጂ! ግጥምንና ዜማን በልዩ ቅላጼ ሕይወት ሰጥቶ በማይረሳና ለዛ በተሞላ የአዘፋፈን ስልት ማቅረብ የሚችል ልዩ ድምፃዊ ነበር ጥላሁን ገሠሠ። ይቅርታ! «ነበር» የሚለው ቃል «ጥላሁን ገሠሠ» ከሚባል ስም ጋር አብሮ አይሄድም! «ነው» ማለቱ ይሻላል። የማይሞተውንና ሁልጊዜም በኢትዮጵያውያን ሕይወትና ስብእና ውስጥ ሲያስተጋባ የሚኖረውን ብርቅ ድምፁን ዘመን ከማይተካቸው ዜማዎቹ ጋር አበርክቶልን ሄዷልና ጥላሁን ገሠሠ ሞተ አይባልም። ይህንን ሃቅ እርሱም ቀድሞ የተረዳው

ይመስለኛል። ከአያሌ ምርጥ ዘፈኖቹ በአንዱ እንዲህ ብሎ አጫውቶን ነበር . . .

**ትንፋሼ ተቀርጾ ይቀመጥ ማልቀሻ**
**ይህ ነው የሞትኩኝለት የኔ ማስታወሻ . . .**
**ውበቷን ሳሞግስ የለምለም ሀገሬን**
**ማንም አይዘነጋም በጩኸት መኖሬን**
**ዜማ እንጉርጉሮዬም የግሌ ቅላጼ**
**ተቀርጾ ይቀመጥ ታሪኬ ነው ድምፄ . . .**
**ያስቀየምኩት ቢኖር የጠላኝ በቁሜ**
**ድምፄን ሰምቶ ያዝናል ለረገፈው አጽሜ**
**እኔን ለበደሉኝ ሰርዣለሁ ቂሜን**
**በኔም የከፋችሁ ይቅር በሉት አጽሜን . . .**

ከጊዜው መርዘም የተነሣ እንዳልሳሳት እሰጋለሁ እንጂ ድሮ ታዳጊ ወጣት እያለሁ ጥላሁን ገሠሠ ብርማ ቀለም የነበራት ቢ. ኤም ደብሊው መኪና ይነዳ እንደነበር ትዝ ይለኛል። ያችን መኪና እያሽከረከረ ሲያልፍ እኔና ጓደኞቼ በደስታ «ጥላሁን! ጥላሁን!» እያልን እጆቻችንን የምናውለበልብለት ንጹሑን የልጅነት ጊዜ አልረሳውም። ታዲያ ያችን መኪና ጥላሁን ገሠሠ እየነዳ የሚያሳይ የቪዲዮ ቅንብር በኢትዮጵያ ቴሌቭዥን ሣምንታዊው «ኅብረ ትርዒት» ፕሮግራም ላይ በተደጋጋሚ ይቀርብ እንደነበረ ትዝ ይለኛል። ጥላሁን ገሠሠ በእግሩና በመኪናው አዲስ አበባን እያሰሰ «ፈልጌ አስፈልጌ . . .» የሚለውን ዜማውን ያቀረበበት ቪዲዮ ነበር። የመጀመሪያው ሙዚቃዊ የቪዲዮ ቅንብር መሆኑ ይሆን?

የቪዲዮን ነገር ካነሣን የጥላሁን ገሠሠን ዕንባ ማን ይዘነጋል? የኢትዮጵያ የፖለቲካ ሁኔታ ትልቅ ማዕበል ውስጥ ሊገባ ባኮበኮበበት ወቅትና የረሀብ አስደንጋጭ መልክ በዓለም ዙሪያ በየጋዜጣው እና በየቴሌቭዥኑ መታየት በጀመረበት ሰሞን የጥላሁንንም ዕንባ አብረን አየነው። ከውስጥ በፈነቀለው ሀዘን ጥላሁን ለወገኑ፥ ለአገሩ ስቅስቅ ብሎ ሲያነባ ተመለከትነው . . . ኢትዮጵያም አብራው አነባች . . .

**ዋይ! ዋይ! ዋይ! ሲሉ**
**የረሀብን ጉንፋን ሲስሉ**
**እያዘንኩኝ ባይኔ አይቼ**
**ምን ላድርግ አለፍኳቸው ትቼ።**
**በዱር አምባ የፈሰሱ ለአቅመ አዳም ያልደረሱ**
**ሁሉም ህጻን ልጆች ናቸው ምንስ ሆኜ ምን ላርጋቸው?**
**ታምር ነው የአምላክ ሥራ**
**ስንቱ ያልቃል ብናወራ**
**አንዱን ጎርፍ አጥለቅልቆት**
**ሌላው ያልቃል በድርቆት**
**በዚች ከንቱ ድልል ዓለም**
**መቼም ጠገብኩ የሚል የለም**
**የተገኘውን እንስጣቸው**
**ቸርነቱን አንንሳቸው . . .**

ጥላሁን ዕንባውን ያፈሰሰበት ሌላም ዘፈን ነበር፥ ለአገሩ ያለውን ፍቅር በዚያ ለእርሱ ብቻ በተ ሰጠው ድምፁ ያንቆረቆረበት . . .

**እንኳንስ ደስታዬን የሰውነቴን ሰው**
**እንኳን ነፃነቴን ፀጋ ክብሬን ትቼው**
**በእናት አገር ምድር በሚያውቀኝ በማውቀው**
**ስቃይ መከራዬን አንቺ ዘንድ ያድርገው።**
**ምድርሽ ላኖረኝ . . . ሰው ላረገኝ ፍቅርሽ**
**ዕድሜዬን ያድርገው ውለታሽን መላሽ**
**ለጥቃትሽ ጋሻ ለችግርሽ ደራሽ . . .**
**ከአድማስ ወዲያ ማዶ ከባሕር ባሻገር**
**በኖርኩበት ምድር እንዲያምርብኝ ባገር**
**እናት አገር ጡትሽ ታሪክ ምድርሽ ይጥራኝ**

**አደራሽን ይዤ ለዐይነ ሥጋሽ ያብቃኝ . . .**

እውነትም ለአገሩና ለወገኖቹ በበቃበት ዕለት ጥላሁን ገሠሠ ይህ ምኞቱ እውን ሆነለት። ተወልዶ እንዳደገባት፥ አድጎና ተከብሮም እንደኖረባት ሁሉ የመጨረሻ እስትንፋሱንም ከአገሩ ምድር፥ ከአገሩ አየር ጋር ተካፈለ። አይደንቅም?

ጥላሁን ገሠሠ ቁምነገር በተሞሉት ዘፈኖቹ አገሩን የሚወድ፥ ለወገኑ የሚቆረቆር ትውልድን ቀርጿል ብል ያጋነንኩ አይመስለኝም። የየዘመኑ ትውልድ ኢትዮጵያዊነቱን አክብሮ እንዲይዝ ጥላሁን ገሠሠ በዘፈኖቹ እያዝናና አስተምሯል፥ እያስተማረም አዝናንቷል። በፍቅር አበድኩ፥ ታወርኩ የሚለውንም ወገኑን ቆም ብሎ እንዲያስተውልና ስለፍቅርም ምንነት እንዲመረምር መጠየቁ አልቀረም . . .

**እባካችሁ ሰዎች ውሰዱኝ ስትሄዱ**
**ፍቅር ጋር መድረሻው በየት ነው መንገዱ**
**ሩቅ ነው ወይስ ቅርብ መኖሪያ መንደሩ**
**ግዴለኝም እኔ ውሎ ለማደሩ**
**ያምራል ወይ በቅርጹ የፍቅር አዳራሽ**
**ቋሚነት አለው ወይ ወይስ ይሆን ፈራሽ?**
**ዙሪያ አጥር አለው ወይ ወይስ ነው ወይ ሜዳ**
**ቦታስ ስፍራ አለው ወይ ማረፊያ ለእንግዳ . . .**

አንዳንድ ጊዜ ሰዎች ስለፍቅር ያላቸው ደግ ያልሆነ አመለካከት እንዲስተካከል በመመኘትም ይመስላል የፍቅርን በጎ ገጽታ እንድንመለከት እንዲህ ያለን . . .

**ሲረዳዱ እኮ ነው ራስ መውደድ ቀርቶ**
**የፍቅር ውጤቱ የሚታየው ጎልቶ**
**ፍቅርን ጨከነ ምነው ማለታችሁ**
**የማይጠፋ ደስታ ሲሰጥ እያያችሁ**
**ክፋት የለበትም ፍቅር እንደሆነ**
**ያመሃኛል እንጂ ሰው ነው የጨከነ**
**በዓለም ላይ አይተናል የሚበቃ አስረጂ**
**ፍቅር እኮ አይደለም ጨካኙ ሰው ነው እንጂ . . .**

የሰው ልጅ ጭካኔም እንዲወገድ ምክር በተላበሱ ዜማዎቹ ሕሊናችንን መሞገቱ አልቀረም . . .

**ፍቅር ከኛ እንዳይለየን እንዲሳካልን ኑሯችን**
**መጨቃጨቅ ይወገድና ሰላም ይሁን ለሁላችን**
**ኑሮ ለሰው ልጆች በእውነት ቀላል ስላለሆነ ዋዛ**
**በሆነው ባልሆነው ይቅር ጭቅጭቃችን አይብዛ**
**ንትርክ ንዝንዝ ካለ በኑሯችን መካከል**
**ወዳጃችንም ይርቃል ሀብትም ቢሆን ይሸሻል . . .**

ለሰው መድኃኒቱ ሰው መሆኑን እንዳንዘነጋም መላልሶ አሳሰቦን ነበር . . .

**ለሀዘን ለፍቅር ለደስታ ለችግር**
**ማነው የሚመረጥ ከሰው . . . ከሰው ወዲያ በምድር**
**የሰው ልጅ በምድር ላይ የታል የተስማማ**
**አንዱ ለፍቶ ሲያገኝ ሌላው እየቀማ**
**እውነት ርኅራኄ ቁምነገር ደግነት**
**እናንተ ነበራችሁ ለሰው ልጆች ሕይወት . . .**

ጥለናት ለምንሄደው ዓለም አንዱ ሌላውን አየረገጠ፥ ኃይለኛው ደካማውን እያጠቃ መኖሩ ደጋግሞ ለፍትኅ እንዲጮህ ሳይገፋፋውም አልቀረም . . .

**ከእንግዲህ ፍረዱኝ ጩኸቴን ስሙና**
**በእውነት ግልጽ ሚዛን ጊዜውን ለኩና**

**ብዙ ጊዜ አልፎኛል መከራዬን ሳይ**
**የኔ ጨኸት ሆኖ ለሌሎች ሲሣይ . . .**

*ይሄኛው ዘፈኑ የጥላሁን ገሠሠን ዘፈኖች ያለፈቃድ እንደልባቸው በሌሎች እያዘፈኑና እያሳተሙ ተገቢውን ዕውቅና እንኳን ሳይሰጡት በአቋራጭ ሀብት ለማካበት ብቻ የሚስገበገቡትን፥ ለገንዘብ እንጂ ለኪነትና ለጥበብ ደንታ የሌላቸውን የዘመናችንን ዘራፊዎች በትዝብት የሚያናግር ሆኖ ነው የተሰማኝ። በእንደዚህ ዓይነቶቹ ሰዎች መጥፎ ሥራ ጥላሁን ቢያዝንም ለራሱ ግን ይሄኛውን ዘፈኑን የሚያንጎራጉር ይመስለኛል . . .*

**መሳቁን ይስቃል ጥርሴ መች አረፈ**
**ልቤ ነው በጣሙን እጅግ ያኮረፈ**
**አልጠፋልህ ብሎኝ የልቤ ውስጥ እሳት**
**ጥርሴ እንዲያምር ብዬ ተወጋሁ ንቅሣት**
**ባዝንም ብደሰትም መሳቄን አልተውም**
**ጥርሴን ፈገግታ እንጂ ሀዘን አይገባውም . . .**

*ንጹሐንን በጉልበታቸው ለሚበድሉ፥ ለሚጎዱ፥ ለሚያስርቡ፥ ለሚያፍኑ፥ ለሚያስሩ፥ ለሚገድሉ ግፈኞች ደግሞ ሰሚ ጆሮና የሚያስተውል ልብ እንዲኖራቸው ጥላሁን ገሠሠ እንዲህ እያለ ይለምንላቸዋል . . .*

**ምስጢሩን ዘርዝረው ገልጸው ሳይረዱ**
**እንዲያው በይሆናል በደል ለፈረዱ**
**አስተካክለው ማየት ማስተዋል ላልቻሉ**
**ይቅር ይበላቸው ምናልባት እንዳሉ**
**በሐሰት ለለወጧት እውነትን ባፋቸው**
**የቁምነገር አምላክ ይቅር ይበላቸው . . .**

*ኢትዮጵያውያንም ራሳቸንን እንድናሻሽል ከድክመታችን ቀንጨብ እያደረገ አወያይቶናል . . .*

**አርቆ ማሰቢያ እያለን አእምሮ**
**እንደምን ተሳነን ለማክበር ቀጠሮ?**
**ቸልተኞች ሆነን ወደኋላ እንዳንቀር**
**በሁላችንም ዘንድ ቀጠሮ ይከበር።**
**ባደጉት አገሮች በሠለጠኑት**
**ደቂቃ ውድ ነች እንኳንስ ሰዐት**
**ስለዚህ እናስብ አንሁን ቸልተኞች**
**ለመሆን እንብቃ ቀጠሮ አክባሪዎች . . .**

*ቀጠሮ! እውነትም ጥላሁን ገሠሠ ከአገሩ ከኢትዮጵያና ከወገኖቹ ኢትዮጵያውያን ጋር የስንብት ቀጠሮ ነበረው። የመጨረሻ እስትንፋሱንና እረፍቱን ከእነርሱ ዘንድ ሊያደርግ ይዞ የነበረውን ቀጠሮ አክብሮ በቃሉ ተገኘ። ለጮኸላትና ዕንባውን ላፈሰሰለት ኢትዮጵያ «መጣሁልሽ» እንዳላት ቃሉን አጥፎ አልቀረም። በሰዐቱ ተገኝቶ ተሰናበታት።*

*መጋረጃውም ተዘጋ . . . ተፈጸመ።*

*መልካም እረፍት ጥልዬ! መልካም እረፍት!*

---

**ቴዎድሮስ አበበ**
Springfield, VA
April 21, 2009